# የተማሪዎን የማንበብ(READ) እቅድ መረዳት

## የማንበብ ህግ(READ Act ) ምንድን ነው?

የአካዳሚክ እድገትን ለማረጋገጥ የኮሎራዶ ንባብ ህግ  (READ) ለሁሉም ተማሪዎች የቅድመ መፃፍ እድገትን ይደግፋል፣ ይህም የK-3 ተማሪዎች ጠንካራ የማንበብ ክህሎት እንዲያዳብሩ በመርዳት ላይ ነው። ይህ የስቴት ተነሳሽነት ሁሉም ተማሪዎች በሦስተኛ ክፍል መጨረሻ በራስ መተማመን አንባቢ እንዲሆኑ የሚያስፈልጋቸውን ድጋፍ እንዲያገኙ ያረጋግጣል። ከ 3 ኛ ክፍል በላይ ያሉ ተለይተው የሚታወቁ ተማሪዎች የክፍል ደረጃ ብቃታቸውን (K-12) እስኪያሚሉ ድረስ በየዓመቱ በንባብ እቅድ ይቀጥላሉ ።

## ተማሪዎች ለንባብ እቅድ እንዴት ይመለመላሉ?

- ከK-3 ክፍል ያሉ ተማሪዎች በስቴት የፀደቀውን የንባብ ግምገማ ይወስዳሉ (Star Early Literacy ወይም Star Reading የሚባሉትን )
- ግምገማው ተማሪዎ ተጨማሪ የንባብ ድጋፍ እንደሚያስፈልገው ካረጋገጠ፣ የተማሪን ማንበብና መፃፍ እድገትን ለመደገፍ ግላዊ የሆነ የንባብ እቅድ ይፈጠራል ።
- ተማሪዎች የምገመገሙበት  ከK-3 ክፍል ብቻ ነው።
- **የንባብ እቅድ( READ Plan) እንደሚያስፈልጋቸው ተለይተው የታወቁ ተማሪዎች የክፍል ደረጃ የማንበብ ብቃት (K-12) እስኪያሳዩ ድረስ በንባብ እቅድ መደገፋቸው ይቀጥላል።**

## የማንበብ እቅድ(READ Plan) ምንን ያካትታል?

- የተማሪው ልዩ የንባብ ጥንካሬዎች እና ማሻሻልያለባቸው ቦታዎች   ላይ ዝርዝር ትንተና
- የተማሪ ፍላጎቶችን መሰረት ያደረጉ የታለመ ትምህርት እና የድጋፍ ስልቶች
- ድጋፉ ውጤታማ መሆኑን ለማረጋገጥ መደበኛ የሂደት ክትትል መረጃ።

የተማሪን የንባብ እድገት ለመደገፍ በቤት ውስጥ ሊጠቀሙባቸው የሚችሉ የትብብር ስልቶች

## ለቤተሰቦች እንዴት ይነገራል?

- የተማሪ ግስጋሴ ማሻሻያ በዓመት ቢያንስ ሶስት ጊዜ ይሰጣል (ህዳር፣ መጋቢት፣ ግንቦት)
- መምህራን ከቤተሰቦቻቸው ጋር በመነጋገር የድጋፍ ስልቶችን ለማስተካከል ይተባበራሉ
- ቤተሰቦች በማንኛውም ጊዜ የተማሪውን እድገት እንዲወያዩ ወይም የሚያሳስባቸውን ነገር ከመምህራቸው ጋር እንዲያካፍሉ ይበረታታሉ

## እንደ የቤተሰብ አጋር የእርስዎ ሚና ምንድን ነው?

: የተማሪዎ የመጀመሪያ እና በጣም አስፈላጊ አስተማሪ እንደመሆኖ፣ የእርስዎ ተሳትፎ ለንባብ ስኬት ወሳኝ ነው። የእርስዎን ግንዛቤዎች ከፍ እናደንቃለን እንደዝሁም ከዝህ በታች ያሉትን እንዲያደርጉ እናበረታታዎታለን፡-

- ስለ ተማሪዎ የማንበብ ፍላጎት እና ተግዳሮቶች አስተያየቶችዎን ያካፍሉ።
- ጥያቄዎችን ወይም ስጋቶችን ከተማሪዎ መምህር ጋር በማንኛውም ጊዜ ተወያዩ
- የተማሪዎን የማንበብ እቅድ በማዘጋጀት እና በመገምገም ላይ ይሳተፉ

ለቤተሰብዎ በሚጠቅም መንገድ የተጠቆሙ የንባብ ስልቶችን በቤት ውስጥ ይተግብሩ. በዚህ የንባብ ጉዞ ላይ እርስዎን እና ተማሪዎን ለመደገፍ የተማሪዎ አስተማሪ እዚህ አለ። ለቀጣይ አጋርነትዎ እናመሰግናለን።